በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰበር መ/ቁ/215321

ግንቦት 2 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ መ/ር ሙሴ አሳየኸኝ --ቀረቡ

ተጠሪ፡ የአ/አ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ -አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ በአስተዳደር አካል የወጣ መመሪያ አግባብነት በፌደራል አስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2013 መሠረት እንዲከለስ የቀረበ አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበዉ አቤቱታ ተጠሪ ነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም ያወጣው የትምህርት አመራሮች ድልድል መመሪያ ህግን ባልተከተለ መልኩ ስለወጣ መመሪያው ተፈፃሚ እንዳይሆን እና እንዲከለስ የሚል ነዉ፡፡የአቤቱታ ይዘትም አመልካች የአለም ብርሃን የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ርዕሰ-መምህር በመሆን ታህሳስ 12 ቀን 2012 ዓ.ም በፌደራል ደረጃ በወጣው የመምህራን እና ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘር የስራ መደብ የድልድል አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 2/2012 መሰረት አድርጎ ጄ.ጂ.ኤ ጥናት አንቀጽ 9 መሰረት ያለውድድር ከነበረበት ርዕሰ መምህር ኬሪየር በደረጃ 18 ተመድቦ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ይሁን እንጂ ተጠሪ ነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም ባወጣው የት/ቤት አመራሮች የድልድል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አፈፃፀም መመሪያ በተመደብኩበት ት/ቤት 1 ርዕሰ መምህር እና 3 ም/ር/መምህር መመደቡ እና የኬርየር ድረጃ ወደ አዲስ ስታንዳርድ የስራ መደብ መቀየሩን ያሳያል፡፡ቀደም ሲል በህዳር ወር የወጣው መመሪያ በታህሳስ በወጣው የፌዴራል የድልድል መመሪያ ተሽሯል፡፡የፌዴራል መመሪያ በሀገር አቀፍ ደረጃ በጂ.ኢ.ጂ ደረጃ የተመደቡ ር/መምህራን ከምደባቸው ላይ ለማንሳት የተደረገ ጥናት ይሁን የወጣ አዲስ መመሪያ በሌለበትና ባልተሻረበት ሁኔታ አመልካች የያዙትን ቦታ/መደብ በተመሳሳይ መደብ መመደብ ሲገባው ቦታውን በነሀሴ ወር 2012 ዓ.ም ባወጣው መመሪያ መሰረት ክፊት ማድረጉ መመሪያን የጣሰ ነው፡፡በዚህ ነሀሴ ወር 2012 ዓ.ም በወጣው መመሪያ መሰረት በክ/ከተማ እና በወረዳው የሚገኙ ር/መምህራን መደቦች ለውድድር እንዲቀርቡ ተደርጎ አመልካች የያዘው ቦታ ለውድድር ክፍት ሆኗል፡፡በመሆኑም ይህ ነሀሴ 2012 የወጣዉ መመሪያ በፌዴራል አስተዳደር አዋጅ ቁ.1183/2011 መሰረት በተጠሪ ድህረ-ገጽ ላይ ያልተጫነ እና ያልተመዘገበ በመሆኑ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ተፈፃሚነት በሌለው መመሪያ መሰረት አመልካች ከተመደብኩበት መደብ እንዲነሳ ሊደረግ አይገባም፡፡ስለዚህ አመልካች የያዝኩት ቦታ ለውድድር ክፍት መደረጉ ተቀባይነት የለውም እንዲባልልኝ፤ተጠሪ ነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም ያወጣው መመሪያ ስነ-ስርዓት ህግን ሳይከተል የወጣ ነው ተብሎ እንዲወሰን፤የተደረገው ውድድር እንዳልተደረገ ተቆጥረው ቀደም ሲል የያዝኩት ደረጃ 18 ላይ እንዲመለስ ተገቢው ካሳም እንዲከፈል እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ ያቀረበው መልስ ነሀሴ 2012 ዓ.ም የወጣው መመሪያ ሀምሌ 28/2012 ዓ.ም ለጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ተልኮ ዐቃቤ ህግም ህዳር 11/2013 ዓ.ም መመሪያ ቁጥር 20/2012 ሆኖ መመዝገቡን አሳውቋል፤በመሆኑም መመሪያ ህግን ተከትሎ የወጣ ስለሆነ አመልካች በቀጥታ ክስ ማቅረብ የሚችሉት ለከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች እንጂ ለዚህ ፍ/ቤት ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፡፡ተጠሪ በአዋጅ ቁ.64/2010 መሰረት መመሪያ የማውጣት ስልጣን አለው፣ መመሪያው ለሁሉም መምህራን እኩል የመወዳደር መብት ያላቸው መሆኑን ይደነግጋል፣ስለሆነም አመልካች ቀድሞ የያዝኩት ቦታ ይሰጠኝ ያሉት ተገቢ አይደለም፣ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ተገቢ ባለመሆኑ ውድቅ እንዲደረግ በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር ከቀረበው ማስረጃ ጋር መርምሮ ተጠሪ መመሪያ የማውጣት ስልጣን አለው፤ ይሁን እንጂ ይህ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 ዓ.ም ከአንቀጽ 6-11 መሰረት መመሪያው ከመውጣቱ በፊት ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም ድህረ-ገጽ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ስለማውጣቱ አልተረጋገጠም፤ረቂቅ መመሪያው ላይም ከሚመለከተው አካል ጋር ውይይት አልተደረገም፣ግብዓት ስለመሰበሰቡ በኋላም ከነማብራሪያው ለፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ስለመላኩ፣ዐቃቤ ህግም ወዲያውኑ መመሪያውን ስለመመዝገቡ ማሳወቅ እንዳለበት አዋጅ 1183/2012 አንቀጽ 16 ያሳያል፣ይሁን እንጂ ተጠሪ ያወጣው መመሪያ በዚሁ መሰረት ስለመወጣቱ አልተረጋገጠም፤ስለዚህ ነሀሴ ወር 2012 ዓ.ም የወጣው መመሪያ እንዲሰረዝ፣ መመሪያው በህጉ መሰረት ተከልሶ እንዲወጣ፣በመመሪያው መሰረት የተደረገው የድልድልም ሆነ ውድድር እንዲሰረዝ፣ተጠሪ ለአመልካች ብር 4000 ኪሳራ እንዲከፍል ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት መዝገቡን መርምሮ አንድ መመሪያ ህጋዊ ስርዓትን ተከትሎ ከወጣ በኋላ መመሪያው ህጋዊ ስርዓትን ሳይከተል ወጥቷል በሚል ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ በህጉ መሰረት ቀርቦ መመሪያው ተፈፃሚ እንዳይሆን ሲደረግ ቀደም ሲል በመመሪያው መሰረት ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች እንደፀኑ የሚቆዩ እንጂ መመሪያው ከመሻሩ በፊት ያሉ የአስተዳደር ውሳኔዎች ሊሰረዙ እንደማይገባ የአዋጅ ቁ/ 1183/2013 አንቀጽ 57/4/ ድንጋጌ ያሳያል፡፡በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መመሪያው ህግን ተከትሎ መውጣት አለመውጣቱን አረጋግጦ ውሳኔ ከመስጠት ባለፈ መመሪያውን መሰረት አድርጎ የተሰጡ ውሳኔዎችም ላይ ገብቶ የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ ሊሽሩ የሚችሉበት አግባብ የለም፤ስለዚህ የስር ፍ/ቤት መመሪያውን ተፈፃሚ እንዳይሆን ውሳኔ ከሰጠበት ቀን በፊት በተጠሪ የተፈፀሙ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች እንዲሰረዙ የሰጠው ውሳኔ የአዋጁን አንቀጽ 57(4)ን ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በከፊል በመሻር መመሪያው ተከልሶ እንደገና እንዲወጣ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡የአቤቱታ ይዘት ባጭሩ፡- አመልካች ለከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበው የአስተዳደር ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ፍ/ቤቱም የፍሬ ነገርና የህግ ጉዳይ መርምሮ የአስተዳደር ውሳኔ ህጋዊ አይደለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፤የአስተዳደር መመሪያ ወይም ውሳኔ እንዲከለስ አቤቱታ የሚቀርበው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል በማለት ይደነግጋል፣በአንቀጽ 49(2) መሰረት የአስተዳደር መመሪያን በተመለከተ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል፣ ስለዚህ ጠቅላይ ፍ/ቤት የመመሪያን ይግባኝ እንጂ የአስተዳደር ውሳኔን ይግባኝ ተቀብሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም፣ ይህንን አልፈው የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ በስር ፍ/ቤት መመሪያው ከመሻሩ በፊት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የተፈፀመውን አስተዳደራዊ ውሳኔዎች እንዲሻር መወሰኑ ስህተት ነው እንዲያርምልን በማለት በስር ፍ/ቤት ያልቀረበውና ክርክር ያልቀረበበት አዲስ ነገር ተቀብሎ የስር ፍ/ቤት መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል፡፡በነሀሴ ወር 2012 ዓ.ም በረቂቅ መመሪያ እንደ ህግና የፀደቀ መመሪያ ቆጥሮ የወሰዳቸው አስተዳደራዊ ተግባራትን ማፅደቅ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡የአስተዳደር ውሳኔዎች ይፀድቃሉ የሚባለው በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መመሪያ ሆኖ ከተመዘገበ በኋላ እንጂ መመሪያው ወደ ኋላ መልሰው መመሪያው ሳይወጣ የተፈፀሙ ተግባራትን ሁሉ እንዲጸኑ ማድረጉ ከአዋጁ መንፈስ እና አላማ ውጪ በመሆኑ ውሳኔው እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ የመጨረሻ ነው ሲል ያቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉን አግባብ ከአዋጅ ቁ.1183/2012 አንቀጽ 49 አንፃር ለማጣራት መዝገቡ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡ለተጠሪ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሶት መልስ ያላቀረበ በመሆኑ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበት ጭብጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘበነዉ አመልካቾች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ መመሪያዉ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 ላይ በተመለከተዉ አግባብ ሥነ ሥርዓቱን ጠብቆ ያልወጣ እንዲሁም ከሌሎች አዋጆች እና በፌዴራል ደረጃ የወጣዉን መመሪያ የሚቃረን ሌላ መመሪያ ስራ ላይ በማዋል ቀደም ሲል በነበረዉ መመሪያ መሰረት ያለዉድድር ተመድበንበት የነበረዉን ቦታ አስለቅቆን ሌሎች ሠራተኞችን የመደበ መሆኑን ሲሆን፣የጠየቁት ዳኝነትም ሥርዓቱን ሳይጠብቅ ተግባራዊ የተደረገዉ መመሪያ እንዲከለስ እና መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የተደረገዉ ምደባም እንዲሰረዝ የሚል ነዉ፡፡

የፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት እና ተጠሪነታቸዉ ለፌዴራል መንግስት የሆነዉ አስፈፃሚ አካላት የሚያወጧቸዉ መመሪያዎች መከተል ያለባቸዉን መርሆዎች እና ሥርዓቶች፣ አንድ መመሪያ ተገቢዉን ሥርዓት ተከትሎ አልወጣም የሚል ማንኛዉም ጉዳዩ የሚመለከተዉ ሰዉ መመሪያዉ እንዲከለስ ዳኝነት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል እና የዳኝነት ጥያቄዉ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሚሰጠዉ ዉሳኔ ወሰኑ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እስከምን ድረስ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡አዋጁ እነዚህንና መሰል ድንጋጌዎችን እንዲያካትት የተደረገበት ምክንያትም የሚመለከተዉ የአስፈፃሚ አካል የሚያወጣዉ መመሪያ ግልጽ የሆኑ ሥነ ሥርዓቶችን ተከትሎ እንዲወጣ እና ይህን ሥርዓት ተከትሎ ያልወጣ ከሆነ ከነግድፈቱ ተፈፃሚ ሆኖ እንዳይቀጥል በማድረግ መንግስታዊ አሠራር ለህዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲከናወን እና በመመሪያዎች አወጣጥ መርሆዎች እና ሥነ ስርዓት ላይ ቅሬታ ያለዉ ሰዉ የመመሪያዎቹን ህጋዊነት በፍርድ ቤት የሚያስመረምርበት ሥርዓትን በመደንገግ አስተዳደራዊ ፍትሕ ማስፈን ነዉ የሚለዉን የአዋጁን አንዱ ዓላማ ገቢራዊ ለማድረግ እንዲቻል ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡አመልካች መመሪያዉ እንዲከለስ ዳኝነት የጠየቁትም በዚሁ መነሻነት ሲሆን፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ ጉዳዩ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ሥርዓቱን ሳይጠብቅ የወጣ ነዉ የሚሉት መመሪያ እንዲከለስ የወሰነ ሲሆን መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የተደረገ ምደባ በሚመለከት ይግባኝ ሰሚዉ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊሰረዝ አይገባም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

በበኩላችንም እንደተመለከትነዉ ስለ ክለሳ ዉሳኔ አሰጣጥ እና አፈፃፀም የሚደነግገዉ የአዋጁ ክፍል አራት ንዑስ ክፍል አራት የዉሳኔ አሰጣጥ በሚለዉ አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ላይ የክለሳ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል ያወጣዉን መመሪያ ሊያጸና ወይም በሙሉ ወይም በከፊል መሻር እንደሚችል እና መመሪያዉን በሙሉ ወይም በከፊል የሻረ እንደሆነ የሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል መመሪያዉን እንደገና እንዲያወጣ ወይም እንዲያሻሽል ማዘዝ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ስለ ክለሳ ዉሳኔ አፈፃፀም በሚያወራዉ አንቀጽ 57 ንዑስ አንቀጽ 3 ስር የክለሳ አቤቱታ የቀረበበት መመሪያ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሻር ከተደረገ በዚያዉ ልክ መመሪያዉ ህጋዊ ኃይል እንደማይኖረዉ በመርህ ደረጃ የሚደነግግ ሲሆን፣የመመሪያዉ በከፊል ወይም በሙሉ መሻር የአስተዳደር ተቋሙ መመሪያዉ ከመሻሩ በፊት በተሻረዉ መመሪያ መሰረት የሰጣቸዉ አስተዳደራዊ ዉሳኔዎቹ እንደጸኑ እንደሚቀሩ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ በአዋጁ ላይ የተመለከተዉን የመመሪያ አወጣጥ ሥርዓትን ተከትሎ አልወጣም በሚል መብት ባለዉ ሰዉ የቀረበለትን የክለሳ አቤቱታ በመቀበል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መመሪያዉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሻር በሚል የሚሰጠዉ ዉሳኔ ዉጤቱ ዉሳኔዉ ከተሰጠ በኋላ የተሻረዉን መመሪያ መሠረት በማድረግ የአስተዳደር አካሉ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ዋጋ እንዳይኖረዉ የሚያደርግ ሲሆን፣መመሪያዉ ከመሻሩ በፊት በሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል በተሻረዉ መመሪያ መሰረት የተሰጠዉን አስተዳደራዊ ዉሳኔ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ዋጋ እንዲያጣ ወይም ተፈፃሚነት እንዳይኖረዉ የማድረግ ዉጤት የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ማንኛዉም ሰዉ ተገቢዉን ሥርዓት ተከትሎ አልወጣም የሚለዉ መመሪያ በፍርድ ቤት እንዲከለስ ዳኝነት ለመጠየቅ መብት ያለዉ ቢሆንም (የአዋጁ አንቀጽ 46/1/ ይመለከቷል)፣ ይህ መብቱ አቤቱታ በቀረበበት መመሪያ መሠረት በአስተዳደር አካሉ የተሰጠ ዉሳኔ እንዲሻር ጭምር መጠየቅን የማያካትት መሆኑን ነዉ፡፡ይልቁንም የአስተዳደር አካሉ መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን ይነካል የሚል ሰዉ መብቱን የሚያስከብረዉ እንደየጉዳዩ ዓይነት ለጉዳዩ አግባብነት ባለዉ ህግ መሠረት የተዘረጋዉን የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት መሠረት በማድረግ ቅሬታዉን ስልጣን ላለዉ አካል በማቅረብ ሊሆን ይገባል፡፡ አዋጁ የመመሪያዉ መሻር ቀደም ሲል በመመሪያዉ መሰረት የተሰጠዉን አስተዳደራዊ ዉሳኔ የመሻር ዉጤት እንደሌለዉ ከላይ በተመለከተዉ አንቀጽ 57(4) ላይ የደነገገበት አንዱ ምክንያት ሊሆን የሚችለዉም እንደየጉዳዩ ባህርይ አንድ የአስተዳደር አካል በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ የሚቀርብበት አካል እና የአቀራረብ ሥርዓቱን በተመለከተ በሌሎች ህጎች ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲከበሩ እና የአንድ አስተዳደር አካል ዉሳኔ ህጋዊነት በሁለት የተለያዩ አካላት ሊታዩ የሚችልበትን ሁኔታ እንዳይኖር ለማድረግም ጭምር እንደሆነ ይታመናል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በዚህ ችሎት ባቀረቡት ቅሬታ አጥብቀዉ የሚከራከሩት መመሪያዉ ከተሻረ መመሪያዉን መሠረት በማድረግ የተደረገ ምደባም መብቴን የሚጎዳ በመሆኑ ተሰርዞ ቀደም ሲል ያለዉድድር ተመድቤበት ወደ ነበረዉ ቦታ ልመለስ ይገባል በማለት ነዉ፡፡ በመሠረቱ ከስራ ምደባና ደረጃ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያለዉ የመንግስት ሠራተኛ ቅሬታዉን የሚያቀርብበትን ሥርዓት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 56/2010 ይደነግጋል፡፡ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓቱ በልዩ ሁኔታ እንዲደነገግ የተፈለገበት ምክንያትም ለቅሬታዎች አፋጣኝ መፍትሔ ለመስጠት፣ ለቅሬታዎች መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ስህተቶችንና ድክመቶችን የማረም እና ሁሉንም የመንግስት ሠራተኞች በእኩልነት ለማስተናገድ የሚያስችል እና ፍትሐዊ የሆነ አሠራር በማስፈን የሰመረ የስራ ግንኙነት እንዲኖር በማሰብ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 75 ይዘት ያስገነዝባል፡፡ በዚህም መሠረት ከስራ ምደባ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያለዉ ሠራተኛ ቅሬታዉን በቅድሚያ ለመስሪያ ቤቱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታዉን ማቅረብ እንዳለበት፣ቅሬታ ሰሚዉ ኮሚቴ በሰጠዉ ፍርድ ቤት ላይ ቅሬታ ካለዉ ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል እና የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ የህግ ስህተት አለዉ የሚል ከሆነም ቅሬታዉን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በማቅረብ መብቱን ማስከበር የሚችል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 77(4)፣ 77፣ 81(1/ሠ) እና 81(5) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ቅሬታዉ በዚህ መልኩ የሚቀርብለት ፍርድ ቤት ህግን የመተርጎም ስልጣን ያለዉ በመሆኑ የምደባዉን አግባብነት ሲመረምር ቅሬታ የቀረበበት ምደባ ለጉዳዩ አግባብነት ያለዉን ህግ መሠረት ያደረገ መሆን ያለመሆኑን ብቻ ሳይሆን ለምደባዉ መሠረት የሆነዉ መመሪያ ስልጣን ባለዉ አካል ተገቢዉን ሥርዓት ጠብቆ የወጣ እና ከሌሎች የበላይ ህጎች (superior laws) ጋር የሚጋጭ መሆን ያለመሆኑን እና ተያያዥ ጉዳዮችን በመመርመር እና ትርጉም በመስጠት የመመሪያዉን ህጋዊ ዉጤት ጭምር በማየት የምደባዉን ህጋዊነት መወሰን ይችላሉ፡፡ በተያዘዉ ጉዳይም አመልካች ምደባዉ መብታችን ይነካል የሚሉ ከሆነ ከፍ ሲል በተመለከተዉ አግባብ ለሲቪል ሰርቪስ ፍርድ ቤት ብሎም ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡ ኖሮ ፍርድ ቤቶቹ የምደባዉን ህጋዊነት ሲመረምሩ ለምደባዉ መሰረት የሆነዉ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 6 እና ተከታዮቹ ላይ የተመለከቱትን የመመሪያ አወጣጥ ሥርዓቶችን ተከትሎ የወጣ መሆን ያለመሆኑን ጭምር መርምረዉ የመመሪያዉን ህጋዊ ዉጤት ወስነዉ ይህን መሰረት በማድረግም በምደባዉ ህጋዊነት ላይ ተገቢዉን መወሰን ይችሉ ነበር፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ከምደባ ጋር በተያያዘ በህግ የተዘረጋዉን ሥርዓት ተከትሎ ቅሬታቸዉን አቅርበዉ መብታቸዉን ማስከበር እየቻሉ፣ በመመሪያ ክለሳ ዳኝነት ሰበብ አስቀድሞ በመመሪያ መሠረት በተጠሪ የተሰጠዉ ምደባ እንዲሰረዝ የሚያቀርቡት መከራከሪያ ተቀባይነት ያለዉ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መመሪያ በአዋጁ የተመለከተዉን ሥርዓት የተከተለ አለመሆኑን አረጋግጦ መመሪያዉ እንዲሻር በማለት፣ በሌላ በኩል መመሪያዉን መሰረት በማድረግ በተጠሪ የተደረገዉ ምደባ ሊሰረዝ አይገባም በማለት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በአዋጁ አንቀጽ 57(4) ላይ የተመለከተዉን ግልጽ ድንጋጌ ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማሻሻል በመ/ቁጥር 208855 ላይ ሐምሌ 27 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**አ/መ** **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**